24ኛ ዓመት ቁጥር 4
24th Year No. 4

ባሕር ዳር የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም
Bahir Dar, March 10, 2019

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 45 ብር
Unit Price Birr 45.

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር 265/2011ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ኮምሽንን ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባሩን መወሰኛ አዋጅ**

## Content

**Proclamation No. 265/2018**

**The Civil Service Commission Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclamation in the Amhara National Regional State.**

## አዋጅ ቁጥር 265/2011ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ኮምሽንን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በቅርቡ የተካሄደውን የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ክለሳና የሀላፊነት ሽግሽግ ተከትሎ ቀደም ሲል የክልሉን የሰው ሀይል ስምሪትና ልማት ሲመራ የቆየው የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የታጠፈ ስለሆነ ዘርፉን ለመከታተልና ለመደገፍ ራሱን የቻለ ምትክ ተቋም መመስረት በማስፈለጉ፤

## Proclamation No. 265/2018

## The Proclamation Issued to Establish the Civil Service Commission and Determine its Powers and Duties in the Amhara National Regional State.

Whereas it is found necessary to establish an independent institution to follow up and assist the sector since the previous civil service and human resource development bureau which was leading the regional human resource operation is abolished following the executive organs organization revision and position redemployment taken place recently,

በክልሉ መንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች ያሉትን ሰራተኞች ወጥነት ባለው መንገድ ለመምራትና እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በተገቢው ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የመንግሥት መስሪያ ቤቶች አደረጃጀት አግባብነትና ውጤታማነት በየጊዜው እያጠና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብና በስራ ላይ ያሉትን መስሪያ ቤቶች የሚያስተዳድር አንድ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ኮምሽን ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 265/2011ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Whereas, it is found necessary to create an organization which enables to lead the employees found in the regional government offices uniformly and to use their knowledge and skills properly,

Whereas, it is found necessary to establish a body which submits a decision proposal for the regional government council by periodically studying the properness of organization of government offices found in the region, effectiveness, and administers the existing offices,

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with the powers Vested in it under Article /49/ sub Articles 3/1/ of the revised Constitution of the National Regional State hereby issued this proclamation.

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "**The Civil Service Commission Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclamation No. 265/2018 in the Amhara National Regional State.**"

## 2. ስለ መቋቋምናተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ኮምሽን ከዚህ በኋላ "ኮምሽኑ" እየተባለ የሚጠራው ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኮምሽኑ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ይሆናል፡፡

## 3. አላማ

የኮምሽኑ አላማ የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ ወጥነት ባለው መንገድ በመምራትና የሰው ሀብቱን በሚገባ በማልማት የመንግሥት ሰራተኞች ህብረተ-ሰቡን በብቃት፣ በታማኝነትና በሀላፊነት ስሜት እንዲያገለግሉ ማድረግ ይሆናል፡፡

## 4. ዋና መስሪያ ቤት

የኮምሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በበታች የክልሉ የአስተዳደር እርከኖች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 2. Establishment

1. The Amhara National Regional State Civil Service Commission hereafter called "the Commission" is established as an independent and having legal personality regional government office in this proclamation.

2. The accountability of the commission shall be to the head of the regional government.

## 3. Objective

The objective of the commission is, by leading the regional civil service uniformly and developing the human resource properly, to make the public servants serve the society in the sence of efficiency, honesty and responsibility.

## 4. Head Office

Whereas the head office of the commission is at Bahir Dar City, it may, as deemed as necessary, establish branch secretariats in the regional government bottom administrational levels.

# ክፍል ሁለት

# የኮምሽኑ ስልጣንና ድርጅታዊ አቋም

## 5. የኮምሽኑ ስልጣንና ተግባር

ኮምሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለክልሉ ነዋሪ ህዝብ የሚሰጠውን መንግሥታዊ አገልግሎት አስመልክቶ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና ደንቦችን ያመነጫል፣ የደምወዝ ስኬልና ልዩ ልዩ አበሎችን አጥንቶ ያስወስናል፤
2. የክልሉን መንግሥት ሠራተኞች የሥራ ውጤት መመዘኛ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
3. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ዘመናዊና የተሟላ የሰብአዊ ሀብት አመራር፣ ትምህርት፣ ሥልጠና፣ ልማትና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱንና በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
4. የክልሉን መንግሥት ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል፣ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ውጤታማና ብቃት ያለው የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፤
5. በተለያዩ የሰው ኃይል ጉዳዮች ላይ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያካሂዳል፤

# PART TWO

# THE POWER AND ORGANIZATION OF THE COMMISSION

## 5. The Powers and Duties of the Commission

The commission, pursuant to this proclamation, has the following powers and duties:

1. Intiates policies, laws and regulations regarding the government service rendered to the regional resident people; causes the determination of salary scales and different perdiems by studying same.
2. Prepares the performance criteria of the regional public servants; and follows up its applicability upon approval.
3. Follows up and supports that modern and complete human resource management, education, training and development is devised and applied in the regional civil service.
4. Maintains the detailed regional public servants profile by registering same; compiles the statistical data, and devises an effective and efficient information system.
5. Carries out research activities on different human power issues.

6. በክልሉ ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ መታገድ፣ በከባድ የዲስፒሊን ቅጣት ከሕግ ውጭ በደምወዝ መያዝ ወይም መቋረጥ፣ በሥራ ምክንያት በደረሰ ጉዳት ሳቢያ የመብት መጓደል ሲያጋጥም ወይም የስራ መልቀቂያንና የአገልግሎት ማስረጃን አስመልክቶ በተወሰዱ እርምጃዎች የሚቀርቡለትን ይግባኞች በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አማካኝነት መርምሮና አጣርቶ በፍሬ-ነገር ደረጃ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፤

6. ለክልሉ ዘላቂ እድገት እርባና ያላቸው አዳዲስ ተቋማት በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲቋቋሙና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነባሮቹ እንደገና እንዲደራጁ፣ በአሠራር እንዲጠናከሩና በተገቢው መንገድ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የውሣኔ ሀሣብ ያቀርባል፡፡

## 6. ድርጅታዊ አቋም

ኮምሽኑ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

1. በርዕሰ-መስተዳድሩ የሚሾሙ ኮምሽነርና ምክትል ኮምሽነር፤
2. እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡፡

## 7. የኮምሽነሩ ስልጣን

1. ኮምሽነሩ የኮምሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር ለኮምሽኑ የተሰጡት ን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፡፡



6. Entertains and renders final decisions on appeals submitted to the civil service administrative court by the regional civil servants with regard to the infringement of rights, as the result of suspension from duty, unlawful withholding or termination of salary due to rigorous disciplinary penalities, or where exists unsufficient rights or with measures taken concerning to clearance and evidence of service.

7. Submits a decision proposal to the regional government council that the regional new institutions that have importance to the regional sustainable development to be established on the basis of study, and wehre it is found necessary, the existing to be re-organized, empowered in procedure and carry out their duties properly.

## 6. Organizational Structure

The commission shall have the following:

1. The commissioner and deputy commissioner appointed by the head of government;
2. As its necessity, other lower heads and workers.

## 7. The Power of the Commssioner

1. The commissioner, being the chief executive officer, implements the powers and duties given to it under Article 6 of this proclamation.

ሀ) የኮሚሽኑን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ለ) የኮሚሽኑን የስራ እቅድና በጀት ረቂቆች ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁለትም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የሰው ሀይል ስምሪቱን አስመልክቶ የጥናትና ምርምር ተግባራት እንዲከናወኑ፣ የስታስቲክስ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና እንዲቀነባበሩ በማድረግ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያስተላልፋል፤

መ) በኮምሽኑ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ሠ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮምሽኑን ይወክላል፤

ሰ) ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በየጊዜው የሥራ ዘገባዎችን ያቀርባል፤

ሸ) ለሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሥልጣንና ተግባሩ ከፊሉን ለበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

A) Leads and coordinates the work of the commssion on top;

B) Prepares the work and budget plans of the commssion and implements upon approval.

C) Conducts research activities concerning human power operation; transfers statistical data to the regional administrative council by causing same to be collected and compiled.

D) Opens and owns bank account in its name.

E) Withdraws money on the basis of budget and work program permitted to the commission; controls its application.

F) Represents the commission for communications taken place with third bodies.

G) Submits periodical report of duties they perform to the regional administrative council.

H) When it finds necessary for work efficency, he may transfer some of the powers and duties to the lower heads through deligation.

## 8. ስለ ምክትል ኮምሽነሩ

1. ምክትል ኮምሽነሩ በኮምሽነሩ አቅራቢነት በርዕሰ- መስተዳድሩ ይሾማል፡፡
2. የምክትል ኮምሽነሩ ተጠሪነት ለኮምሽነሩ ይሆናል፡፡
3. ምክትል ኮምሽነሩ፡-

ሀ/ በኮምሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

ለ/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 9. ስለ በጀት

የኮምሽኑ በጀት በክልሉ መንግሥት ይመደባል፡፡

## 10. ስለ ሂሣብ መዛግብትና ኦዲት

1. ኮምሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡
2. የኮምሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት-ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ፡፡

## 8. The Deputy Commissioner

1. The deputy commissioner is appointed by the head of government through the submission of the commissioner.
2. The accountability of the deputy commissioner is to the commissioner.
3. The deputy commissioner:

A/ Carries out activities particularly given to him by the commissioner.

B/ Work on behalf of the commissioner when he is absent or unable to carry out his duties.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 9. Budget

The budget of the commission is allocated by the regional government.

## 10. Book of Account and Audit

1. The commission maintains complete and accurate book of accounts.
2. The book accounts and money as well as property documents of the comssion shall be audited by the regional auditor general or other auditors assigned by it.

## 11. ተፈፃሚነት ስለ ማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 12. መብቶችና ግዴታዎችን ስለ ማስተላለፍ

የሲቪል ሰርቪሱን የሰው ሀይል ስምሪትና አስተዳደር በተመለከተ ስራ ላይ በቆየው አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተላልፈዋል፡፡

## 13. ደንብ የማውጣት ስልጣን

ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ኮምሽኑ ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሰረት ለሚወጡት ደንቦች ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ያወጣል፡፡

## 11. Inapplicable Laws

Any law, regulation, directive or customary practice inconsistent with this proclamation, may not apply to matters provided for therein.

## 12. Transferring Rights and Obligations

The rights and obligations given to the regional civil service and human resource development bureau under proclamation No. 230/2016 concerning the civil service human power operation and administration are transferred to the newly established regional civil service commission.

## 13. Power to Issue Regulation

The regional administrative council may issue regulations necessary for the full implementation of this proclamation.

## 14. Power to Issue Directives

The commission may issue directives necessary for the full implementation of provisions for this proclamation and regulations to be issued following this proclamation.

## 15. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*ባሕር ዳር*

*የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም*

*ገዱ አንዳርጋቸው*

*የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚደንት*

## 15. Effective Date of the Proclamation

This proclamation shall come into force as of the date of its official publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

**Done at Bahir Dar,**

**This 10th Day of March, 2019**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Regional State**